## የጋራ አካፋይ እና የጋራ ብዜት የቃላት ጥያቄዎች፡

### ጥያቄ አንድ

1. ሄኖክ በሚገለገልበት የእስፖርት ማዕከል ውስጥ በየ 6 ቀን ዋና ቢዋኝ፣ በየ 4 ቀን ቢሮጥ እና በየ 16 ቀን ደግሞ ሳይክል ቢነዳ እነዚህን እንቅስቃሴዎች ከዛሬ ጀምሮ መስራት ቢጀምር በስንተኛው ቀን ላይ ሁሉንም እንቅስቃሴዎች በአንድ ቀን ላይ ሊሰራ ይችላል ?

2. ሄለን 14 ነጭ ፣ 12 ቫኒላ እና 8 እስትሮበሪ ቸኮሌቶችን በካርቶኖች ውስጥ ማስቀመጥ ፈለገች፡፡ በእያንዳንዱ ካርቶን ውስጥ እኩል መጠን ቸኮሌቶችን ማስቀመጥ ቢኖርባት ሁሉንም ቸኮሌቶች አስቀምጣ ለመጨረስ ስንት ካርቶኖች ያስፈልጋታል ?

3. በአካባቢያችን በሚገኝ የአትክልት ስፍራ 45 የካሮት፣ 81 የድንች እና 63 የቲማቲም ችግኞችን ለመትከል ታስቧል፡፡ በአንድ መስመር ላይ መትከል የሚቻለው አንድ አይነት ችግኝ ብቻ ቢሆን በአንድ መስመር ላይ በትልቁ መትከል የሚቻለው የችግኝ ቁጥር ስንት ነው ?

4. ትምህርትቤታችን አጠገብ የሚገኘው ሱቅ ውስጥ አንድ እሽግ እርሳስ 6 እርሳሶችን፣ አንድ እሽግ ደብተር ደግሞ 8 ደብተሮችን ይይዛል ፡፡ እኔ ደግሞ እኩል እርሳስ እና ደብተር እንዲኖረኝ ብፈልግ በጠቅላላው ስንት እሽግ እርሳስ እና ስንት እሽግ ደብተር መግዛት ይኖርብኛል ?

   .................................. እሽግ እርሳስ .................................. እሽግ ደብተር

5. ሳምራዊትን ልደት ለማክበር በአካባቢያችን የሚገኝ የገበያ ማዕከል ውስጥ 20 ፊኛዎች ፣ 10 ጡሩንባዎች እና 8 ከረሜላዎች በእሽግ ይሸጣል ፡፡ ከሁሉም ዓይነት እኩል እኩል መግዛት ብንፈልግ ከእያንዳንዱ እቃ ስንት ስንት እሽግ መግዛት ይኖርብናል ?

   ........................ እሽግ ፊኛዎች ...................... እሽግ ጡሩንባዎች ......................... እሽግ ከረሜላዎች

LIVEWORKSHEETS

6. ሚኪ  ሁልጊዜ በየ 7 ቀን ዋና ይሄዳል ሳሮን ደግሞ ሁልጊዜ በየ 5 ቀን ዋና የምትሄድ ቢሆን ሁለቱም በአንድ ቀን ዋና ቦታ የሚሄዱት በስንተኛው ቀን ላይ ነው ?

7. እቤታችን ውስጥ ያሉንን 15 ማንጎዎች፣ 9 ብርቱካኖች እና 18 ሎሚዎች በቅርጫት ውስጥ ለማስቀመጥ ፈለግን ። ሁሉንም ፍራፍሬዎች ሳናቀላቅል እኩል እኩል በማድረግ በቅርጫቶች ውስጥ ለማስቀመጥ ብንፈልግ በአንድ ቅርጫት ውስጥ ስንት ፍሬዎችን ማስቀመጥ እንችላለን ? ፈራፍሬዎቹን ለማስቀመጥ ስንት ቅርቻቶች ያስፈልጉናል ?

...................... ፍሬዎችን ...................... ቅርጫቶች

8. ከሰፈራችን ወደ ፒያሳ ለመሄድ ሸገር አውቶቡስ በየ 6 ደቂቃ የምትመጣ ሲሆን አንበሳ አውቶቡስ ደግሞ በየ 8 ደቂቃ የምትመጣ ቢሆን ሁለቱም አውቶቡሶች በስንተኛው ደቂቃ በአንድላይ የመጣሉ ?

9. አንድ ቢጫ እና አንድ አረንጓዴ የክሪስማስ አምፖሎች እኩል መብራት ጀምረው ቢጫ አምፖሉ በየ 4 ሴኮንድ የሚበራ የሚጠፋ  ሲሆን አረንጓዴ አምፖል  ደግሞ በየ 6 ደቂቃ ይበራል ይጠፋል ። ሁለቱም አምፖሎች በስንተኛው ደቂቃ ላይ እኩል የበራሉ ?

10. ሳም ለክፍል ጓደኞቹ ለማከፋፈል 39 እርሳሶች እና 26 እስከርቢቶች አሉት? ለእያንዳንዱ ተማሪ ተመሳሳይ መጠን ያለው እስከርቢቶ እና እርሳስ መቀበል አለበት እና ምንም እስክሪብቶ ወይም እርሳሶች አይተርፉም።. በዚያ ክፍል ውስጥ ከፍተኛው የተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

11. ሄኖክ በኪሱ 12 ብር ፣  ሳሚ ደግሞ 15 ብር  አለው። ሁለቱም ለአንድ ጓደኛቸው ካላቸው ገንዘብ ላይ ከፍተኛውን እና እኩል መጠን ገንዘብ መስጠት ይፈልጋሉ.። ገንዘቡን ከሰጡ በኋላ ሄኖክ እና ሳሚ የሚቀራቸው የገንዘብ መጠን ስንት ይሆናል ?

ሳሚ ...................... ብር ሄኖክ ................... ብር

LIVEWORKSHEETS